## የራብ ቀጠሮ (ከያሬድ ተሾመ ኖርዌ)

በ አስር- ዓመት ነው አለን በልዩሽ፣
የብር-አንባር ቀጠሮ የጋብቻ መዝሙርሽ፣
... የአዓግም አኬል-ዓማ ጥሪሽ፣
... የጥቁር አክሊል መድፋትሽ፣
... ሚደርስ ክፉ ስጠታሽ።

አሁን ነው አለን ቀመሩ፣
ያ ገዢ ያ ሊቅ መምሩ፣
ቢመቸው ያ ግፍ ወንበሩ፣
ሰመረ ይለናል ነገሩ፣
የቀን ሰሌት ድምሩ፣
... የጉዘት የራብ ድምሩ፣
... የንግርት የጀግራፊሩ፣
... የርዛት የቸነፈሩ፣
... "ልክ ነው" አለ ቀመሩ።

በዘንድሮ ነው አሉን መሀላው፣
መመቻው ያዘን ከበሮ፣
በተፈጥሮሽ የውል ቋጠሮ፣
... የፍሬሽ ዘር የቡቃያው፣
... በጽንስ ነቱ የሚቀረው፣
... ደመናው ሞት የሚያጠላው፣
... የፈቃድ ፊርማሽ አሁን ነው።

ባስር ዓመት ሆነ በልዩሽ፣
የጠቢቦች ቀመር ንግርትሽ፣
የዞድያክ ተራ ኮከብሽ፣
... ያዋቂ የይትባህልሽ።

ታዲያ! ... እንደምን አመኑ ልጆችሽ?
ውስጥሽን ገዝግዞ የበላሽ፣
ያገዳው ትል የሆድ አራሽ፣
ተከማችቶ ባካል ጉያሽ፣
ተልቶ ተልቶ እየበላሽ፣
አድጓል ሲለን ኢኮኖሚሽ..!